# በአራዳ ክፍል ከተማ ትምህርት ጽ/ቤት

## የ6ኛ ክፍል የአንደኛ ደረጃ ትምህርት ማጠናቀቂያ ሞዴል ፈተና

## ሒሳብ ጥር 2016 ዓ.ም/ Jan2024

**የጥያቄው ብዛት** ፦30 **የተፈቀደው ሰዐት፦1ሰዐት**

አጠቃላይ ትዕዛዝ

ይህ የሒሳብ ፈተና ነው፡፡በዚህ ፈተና ውስጥ 30 ጥያቄዎች ተካተዋል ለእያንዳንዱ ጥያቄ ትክክለኛ መልስ የሆነውን አማራጭ የያዘውን ፊደል በመምረጥ ለመልስ መስጫ በተሰጠው ወረቀት ላይ በማጥቆር መልስ ይሰጣል፡፡ በፈተናው ላይ የተሰጡትን ትዕዛዞች በጥንቃቄ በማንበብ ፈተናውን መስራት ይጠበቅባችኋል፡፡ መልስ የሚሰጠው ለብቻ በተዘጋጀው የመልስ መስጫ ወረቀት ላይ ነው፤ በመልስ መስጫው ላይ ትክክለኛውን መልስ በማጥቆር የሚመለስ ሲሆን የሚሰራው በእርሳስ ብቻ ነው፤ ትክክለኛው መልስ በማጥቆር ሲሰራ ለማጥቆር የተፈቀደው ቦታ በሙሉ በሚታይ መልኩ በደንብ መጥቆር አለበት ፤ የጠቆረውን መልስ ለመቀየር ቢፈለግ በፊት የጠቆረውን በደንብ በማጥፋት መጽዳት አለበት፡፡

መልስ የሚሰጠው በመልስ መስጫው ላይ ብቻ ነው ለምሳሌ መልሳቹ **ለ** ከሆነ ከታች በሚታየው መልክ ማጥቆር አለባችሁ

| ሀ | ለ | ሐ | መ |
|---|---|---|---|
| ○ | ● | ○ | ○ |

ፈተናውን ሰርቶ ለመጨረስ የተፈቀደው ሰአት **1**ሰአት ነው፡፡ ፈተናውን ሰርቶ ለመጨረስ የተሰጠው ሰአት ሲያበቃ ለመስሪያነት የምንጠቀምበትን የመጻፊያ እርሳስ ማስቀመጥ እና ፈተናውን መስራት ማቆም አለብን፡፡ ፈተናው እንዴት እንደሚሰበሰብ በፈታኙ/ኟ እስከሚነገር ድረስ በቦታችን ተቀምጠን መጠበቅ አለብን፡፡

መኮረጅ ወይም በፈተና ሰአት የፈተናን ህግ የማያከብር ተፈታኝ ፈተናው አይያዝለትም ፤ፈተናውን እንዳይፈተንም ይደረጋል፡፡

ፈተናውን መስራት ከመጀመራችሁ በፊት በመልስ መስጫው ላይ መሞላት የሚገባቸውን መረጃዎች በሙሉ በጥንቃቄ መሞላት አለባችሁ፡፡

**ፈተናውን መስራት ጀምሩ ሳይባል መጀመር አይፈቀድም !**

**ለሚከተሉት ጥያቄዎች ከቀረቡላቸው አማራጮች መካከል ትክክለኛውን መልስ የያዘውን ፊደል ብቻ በመምረጥ በተዘጋጀው መልስ መስጫ ወረቀት ላይ አጥቁሩ።**

1) ከሚከተሉት ውስጥ እውነት የሆነው የቱ ነው?

ሀ) አንድ ቁጥር በ5 ተካፋይ ከሆነ በ10 ተካፋይ ነው።

ለ) አንድ ቁጥር በ4 ተካፋይ ከሆነ በ6 ተካፋይ ነው።

ሐ) አንድ ቁጥር በ3 ተካፋይ ከሆነ በ9 ተካፋይ ነው።

መ) አንድ ቁጥር በ10 ተካፋይ ከሆነ በ5 እና በ2 ተካፋይ ነው።

2) አንድ ሙሉ ቁጥር በ 2 እና በ3 ተካፋይ ከሆነ ከሚከተሉት ውስጥ በየትኛው ተካፋይ ይሆናል

ሀ) በ4 ለ) በ6 ሐ) በ3 መ) በ8

3) አንድ ሙሉ ቁጥር በ9 ተካፋይ የሚሆነው ከሚከተሉት ውስጥ የቱን ሲያሟላ ነው

ሀ) የሆሄያቱ ድምር በ3 ተካፋይ ከሆነ

ለ) የሆሄያቱ የአንድ ቤት ሆሄ 0 ከሆነ

ሐ) የሆሄያቱ ድምር በ9 ተካፋይ ከሆነ

መ) የሆሄያቱ የአንድ ቤት ሆሄ 3 ከሆነ

4) ሀእና ለ ሙሉ ቁጥሮች ቢሆኑ" ለ" የ" ሀ" አካፋይ ወይም ትንትን ነው የምንለው አንድ ሙሉ ቁጥር መ ሲኖር ነው እና ከሚከተሉት የትኛው ፎርም ሲሟላ ነው

ሀ) ሀ=ለ×መ ለ) ሀ=ለ+መ ሐ) ሀ=ለ-መ መ) ሀ= ለ÷መ

5) አንድን የተሰጠ ሙሉ ቁጥር ያለ ቀሪ የሚያካፍሉ ሙሉ ቁጥሮች የቁጥሩ ________ ይባላሉ ከሚከተሉት ውስጥ ክፍተቱን የሚሞላ የቱ ነው

ሀ) ድምር ለ) አካፋይ ሐ) ብዜት መ) ልዩነት

6) ከአንድ የሚበልጥ ማንኛውም ሙሉ ቁጥር ተካፋይነቱ በአንድ እና በራሱ በቁጥሩ ብቻ ከሆነ ሙሉ ቁጥሩ _______ ይባላል።

ሀ) አክታሚ ለ) ኢ_አክታሚ ሐ) ብቸኛ መ) ተተንታኝ

7) አንድ ሙሉ ቁጥር ለሁለት ወይም ከሁለት በላይ ለሆኑ ሙሉ ቁጥሮች አካፋይ ከሆነ ሙሉ ቁጥሩ ከሚከተሉት የትኛው ይባላል?

ሀ) የጋራ ብዜት ለ) ብዜት ሐ) አካፋይ መ) የጋራ አካፋይ

8) አንድ ሙሉ ቁጥር ለሁለት ወይም ከሁለት በላይ ለሆኑ ሙሉ ቁጥሮች ብዜት ከሆነ ሙሉ ቁጥሩ ከሚከተሉት የትኛው ይባላል?

ሀ) የጋራ ብዜት ለ) ብዜት ሐ) አካፋይ መ) የጋራ አካፋይ

9) ሁለት ተማሪዎች ከቤት ወደ ት/ቤት ሁል ጊዜ ይሄዳሉ። አንደኛው ከቤት ወደ ት/ቤት ለመሄድ 20 ደቂቃ ይፈጅበታል። ሁለተኛው ደግሞ 30 ደቂቃ ይፈጅበታል። ሁለቱ ተማሪዎች ጠዋት ከቤት ወደ ት/ቤት እኩል ቢነሱ ፣ በሁለተኛ ጊዜ እኩል ከቤት የሚነሱት ከስንት ደቂቃ በኃላ ነው?

ሀ) 20　　ለ) 30　　ሐ) 50　　መ) 60

10) አንድን ክፍልፋይ በዝቅተኛ ሂሳባዊ ቃል ለመግለፅ ከሚከተሉት ውስጥ ትክክል የሆነው የቱ ነው?

ሀ) የላዕሉን ና የታህቱን ትልቁን የጋራ አካፋይ መፈለግ

ለ) ላዕሉንና ታህቱን በት.ጋ.አ ማካፈል

ሐ) ሀእናለ መልስ ናቸው

መ)ሁሉም መልስ ናቸው

11) ድብልቅ ቁጥሮችን ወደ አስርዮሽ ለመለወጥ ላዕሉን በታህቱ ______እና ሙሉ ቁጥሩን ______ ያስፈልጋል።

ሀ) ማባዛትና መደመር　　ለ) ማካፈልና መደመር

ሐ) መደመር እና ማባዛት　　መ) መደመርና ማካፈል

12) ላዕሉ በታህቱ በሚካፈልበት ወቅት የመጨረሻ ቀሪ 0 የሆነና የማካፈሉም ሂደት መጨረሻ ያለው ከሆነ አስርዮሻዊ ቁጥሩ ______ ይባላል።

ሀ) ኢ-አክታሚ　　ለ) አክታሚ　　ሐ) ብቸኛ　　መ) ድብልቅ

13) 0.345 ወደ መቶኛ ስንለውጠው አስርዮሽ ቁጥሩን በስንት ማባዛት ይኖርብናል?

ሀ) በ10　　ለ) 1000　　ሐ) 100　　መ) 10,000

14) 4.321 ወደ ክፍልፋይ በሚለወጥበት ወቅት ታህቱ የሚሆነው ከሚከተሉት ውስጥ የቱ ነው?

ሀ) 100　　ለ) 1000　　ሐ) 10　　መ) 10,000

15) መቶኛን ወደ ክፍልፋይ ስንለውጥ መጀመሪያ (%) የሚለውን ወደ ______ መለወጥ አለብን ከሚከተሉት ውስጥ (%) የትኛውን ይወክላል?

ሀ) $\frac{1}{10}$　　ለ) $\frac{1}{1000}$　　ሐ)$\frac{1}{100}$　　መ) $\frac{1}{10000}$

16) መቶኛን ወደ አስርዮሽ ስንለውጥ ቁጥሩን በ $\frac{1}{100}$______ እናደርጋለን ከሚከተሉት ውስጥ ትክክል የሆን የቱ ነው?

ሀ) ማካፈል　　ለ)ማባዛት　　ሐ) መደመር　　መ) መቀነስ

17) ሁለት የተለያዩ ታህት ያላቸው ክፍልፋዮችን ለማወዳደር የመጀመሪያውን ክፍልፋይ ላዕል ከሁለተኛው ክፍልፋይ ታህት ጋር ________ እና በተመሳሳይ የመጀመሪያውን ክፍልፋይ ታህት በሁለተኛው ክፍልፋይ ላዕል ጋር________ በማድረግና ማወዳደር ይቻላል:: በክፍተት ቦታው የሚገባው መሰረታዊ ስሌት የትኛው ነው?

ሀ) መደመር ለ) መቀነስ ሐ) ማካፈል መ)ማባዛት

18) ክፍልፋዮችን ለማወዳደር ______ ተመሳሳይ መሆን አለበት ከሚከተሉት ውስጥ የትኛው በክፍተት ቦታው ይሞላል?

ሀ) ታህታቸውን ለ) ላዕላቸውን ሐ) ሁለቱንም መ) መልሱ አልተሰጠም

19) $\frac{4}{6}$፣ 0.3፣ 20% ፣ 0.42 ከትንሹ ወደ ትልቁ በቅደም ተከተል የተቀመጠው ከሚከተሉት ውስጥ የትኛው ነው?

ሀ) $\frac{4}{6}$፣ 0.3፣ 20% ፣ 0.42 ለ) 20%፣0.3፣0.42፣$\frac{4}{6}$

ሐ) 20%፣4/6፣0.3፣0.42 መ) $\frac{4}{6}$፣20%፣0.3፣0.42

20) አንድ ት/ቤት ውስጥ 600 ወንድ እና 400 ሴት ተማሪዎች ይገኛሉ በዚህ ትምህርት ቤት ውስጥ የሴት ተማሪዎች በፐርሰንት ሲገለፅ ከሚከተሉት ውስጥ የትኛው ነዉ?

ሀ) 60% ለ) 30% ሐ) 40% መ) 400%

21) አንድ ባለሱቅ የተለየያዩ ሸቀጦችን በብር 800 በብር ገዝቶ በብር 1700 ብር ቢሸጠው ባለ ሱቁ ምን ያህል ገንዘብ በፐርሰንት አተረፈ?

ሀ) 102.5% ለ) 112.5% ሐ) 80% መ) 90%

22) ሁለት ታህታቸው የተለያየ ክፍልፋዮችን በምንደምርበት ወቅት ከሚከተሉት ውስጥ የትኛውን ተመሳሳይ ማድረግ አለብን?

ሀ) ታህታቸውን ለ) ላዕላቸውን

ሐ) ሁለቱንም መ) ላዕሉን ከላዕሉ ታህቱን ከታህቱ መደመር

23) ቀነኒሳ በቀለ ለሁለት ሳምንት የተለያዩ እንቅስቃሴዎችን ያደርጋል:: በመጀመሪያ ሳምንት

$4\frac{6}{3}$ሰዓት ልምምድ ቢያደርግ:: በሁለተኛው ደግሞ 4.32 ሰዓት ልምምድ ቢያደርግ በአጠቃላይ ለልምምድ ምን ያህል ሰዓት ይፈጅበታል?

ሀ) 10 ለ) 1.32 ሐ) 10.32 መ) 22.32

24) $3\frac{6}{4}-2.45$ ከሚከተሉት አማራጮች ውስጥ ልዩነቱ የሆነው የቱ ነዉ?

ሀ) 1.05　　ለ) 2.05　　ሐ) 3.05　　መ) 2.54

25) በአንድ ባልዲ ውስጥ $4\frac{3}{4}$% ቆርኪዎች ነበሩ አማኑ ከነበሩት ቆርኪዎች ውስጥ 2.75% ቆርኪዎችን ወሰደ። በባልዲው ውስጥ ምን ያህል ቆርኪዎች ይቀራሉ?

ሀ) 3%　　ለ) 4%　　ሐ) 2%　　መ) 1%

26) አንድ የእህል ነጋዴ 100,000 ብር የገዛውን ጤፍ 110,000 ብር ቢሸጠው ነጋዴው ያገኘው ትርፍ በፐርሰንት ስንት ነው?

ሀ) 10%　　ለ) 20%　　ሐ) 15%　　መ) 25%

27) አልማዝ ታታሪ ተማሪ ናት ለማጠቃለያ ፈተና ዝግጅት ማጥናት ፈልጋ እቅድ አወጣች።ካወጣችው እቅድ ውስጥም የመጀመሪያ ቀን ለ $3\frac{4}{2}$ ሰዓት ማንበብ ነው ይህንን እቅድ ለ አንድ ሳምንት ደጋግማ መጠቀም ፈለገች አልማዝ በሳምንቱ መጨረሻ ላይ ለማጥናት ምን ያህል ሰዓት ይፈጅባታል።

ሀ) 26ሰዓት　　ለ) $\frac{10}{2}$ሰዓት　　ሐ) 35ሰዓት　　መ) $\frac{2}{10}$ሰዓት

28) በአንድ ክፍል ውስጥ 63 ተማሪዎች አሉ በዚህ ክፍል ውስጥ እኩል ተማሪ ያለበት ቡድን ለማስቀመጥ ተፈለገ እና በክፍል ውስጥ ከ8 ያነሰ ቡድን እንዲኖር ተፈለገ በዚህ ክፍል ውስጥ እኩል ተማሪ ያለበት ስንት ቡድን ይኖራል?

ሀ) 6 ቡድን　　ለ) 7ቡድን　　ሐ) 8ቡድን　　መ) 9ቡድን

29) ከሚከተሉት ውስጥ ትክክል ያልሆነው የቱ ነው?

ሀ) መደመር የቅይይር ባህሪ ይሰራል

ለ) ማዛት የቅይይር ባህሪ ይሰራል

ሐ) ማካፈል የተጣማጅነት ባህሪ ይሰራል

መ) መደመር የተጣማጅነት ባህሪ ይሰራል

30) አንድ መኪና በ5 ሰዓት ውስጥ 1000.5 ኪ.ሜ ቢጓዝ በ1 ሰዓት ውስጥ ምን ያህል ኪ.ሜ መጓዝ ይችላል?

ሀ) 100.1 ኪ.ሜ　　ለ) 200.1ኪ.ሜ

ሐ) 500.1ኪ.ሜ　　መ) 2000.1ኪ.ሜ